# ቢቢሲ የሚሰራው ለማን ነው?-ተቃዋሚዎቻችንስ?

**ዘአማን ብሩክ - ከአዲስ አበባ**

"… ቢ.ቢ.ሲ ካለፈው ስህተቱ የተማረ አይመስልም፡፡ ዛሬም ለሁለተኛው ጊዜ ደገመው፡፡ …" ይላል- ሰሞኑን በአይጋ ፎረም ጽሬ - ገጽ ላይ የቴሌቪዥን ጣቢያውን ሐሰተኛ ዘገባ አስመልክቶ አቶ ብርሃነ ካሕሳይ በተባሉ ሀገር ወዳድ ግለሰብ የቀረበ ጽሑፍ፡፡ እርግጥ የፀሐፊው መነሻ ቢ.ቢ.ሲ ሰሞኑን ያስራጨው ሚዛናዊ ያልሆነ፣ ወገንተኛና የእውነት እንጥፍጣፊ የሌለው ብሎም እንደወትሮው ምንም ዓይነት ተጨባጭ ማስረጃ ሳይኖረው የኢትዮጵያን መንግስት ስም ለማጥፋት የተወጠነ አስገራሚ ዘገባ ነው፡፡ታዲያ የፀሐፊውን ትክክለኛ ዕይታ ሙሉ በሙሉ በመቀበል፤ እኔም "ቢ.ቢ.ሲ የሚሰራው ለማን ነው? ተቃዋሚዎቻችንስ?" የሚል ጥያቄን በማንሳት ብዕሬን ከወረቀት ጋር እንዲህ አዋድጄዋለሁ። መልካም ንባብ፡፡…

ሰሞነኛው የቢ.ቢ.ሲ ዘገባ ይዘቱ እንደ ሁልጊዜው ቢሆንም፤ አቀራረቡ ግን ትንሽ ቀየር ያለ ይመስላል፡፡ ይኸውም ለወትሮ በእነ ሂዩማን ራይትስ ዎች ሆን ተብለው የሚቀናበሩ የጥላቻ መግለጫዎችን ቀዳሚ ሆኖ ያነበንብ ነበር፡፡ በዚህም የአክራሪ ኒዮ - ሊበራሎች አፈ - ቀላጤ እስከመሆን ድረስ የዘለቀ ጣቢያ ነው፡፡

የዘንድሮው ግን የተለየ ነው፡፡ "ጋዜጠኞቼን ወደ ኢትዮጵያ በቱሪስት መልክ በመላክ የምርመራ ጋዜጠኝነትን ዘዴ ተጠቅሜ ያገኘሁት መረጃ ነው" በማለት የእርዳታ እህል ለፖለቲካ ጥቅም እየዋለ ነው ሲል የተለመደ ቅጥፈቱን የቀጠለው የየትኛውንም ተቋም መግለጫ ሳይጠብቅ በራሱ ተነሳሽነት መሆኑን ይፋ አድርጓል፡፡ ታዲያ ይህ አባባሉ 'ቢ.ቢ.ሲ የማንን ተግባር እየተወጣ ነው?' የሚል ጥያቄ ማጫሩ የሚቀር አይመስለኝም።

እንደሚታወቀው ቢ.ቢ.ሲ በእንግሊዝ ህዝብ ታክስ የሚተዳደርና በዋነኛነትም አገልግሎት የሚሰጠው ለዚሁ ዜጋ ነው፡፡ ይሁንና የዕርዳታ እህል አሰጣጥን በተመለከተ በየዓመቱ የቤተክርስቲያን ስዕለት ያለበት ይመስል በሀገራችን ላይ

የሚነዛው አሉባልታ፤ ተግባሩን እየተወጣ ያለው ለሌላ "ኃይል" መሆኑን ለመገንዘብ አይከብድም።

እነ ሂዮማን ራይትስ ዎችን የመሳሰሉ ፅንፈኛ ሃይሎች የህዝቡን ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤትነት በመጋፋት የራሳቸውን ተላላኪዎች (በተለይም የመድረክ አመራሮችን) "ዙፋን ለማስነገስ" በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ ጣልቃ ለመግባት በተደጋጋሚ ያደረጉት ጥረት በዴሞክራሲያዊ ምርጫ በሚያምነው ሚዛናዊው የኢትዮጵያ ህዝብ አማካኝነት ከሽፏል፡፡ በዚህም አክራሪ ኒዮ - ሊበራሎቹን "ከሉዓላዊ ስልጣኔ ላይ እጃችሁን አንሱ!" የሚል ግልፅና የማያወላዳ ምላሽ ሰጥቷቸዋል፡፡

ሆኖም እነ ሂዮማን ራይትስ ዎች አርፈው አልተቀመጡም፡፡ የ"እንጋሽነት" ምኞታቸው ሲጨነግፍባቸው በሦስት ወር ልዩነት "በሰብዓዊ መብት" ሽፋን በሀገራችን ላይ የውሸት መግለጫ ጋጋታ ያዥጎደጉዱ ጀመር፡፡ ዋነኛ ዓላማቸውም ከሊበራሊዝም ርዕዮተ - ዓለም ውጪ በራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ፈጣንና ተከታታይ በሆነ መልኩ የሚያድጉ ሀገራትን ማጣጣል በመሆኑም፤ እንደ ቢቢሲ ዓይነቱን የኒዮ - ሊበራሊዝም አቀንቃኝ ሚዲያዎችን በግንባር ቀደምትነት ሲጠቀሙ ቆይተዋል፡፡ ለዚህም ከምርጫ 2002 በፊትና በኋላ "ጫና መፍጠሪያ አንድ መቶ መንገዶች" ፣ "ለፖለቲካ መሣሪያ የሚውለው እርዳታ" ወዘተ. የሚሉ የሂዩማን ራይትስ ዎች የፈጠራ ሪፖርቶችን ያለ ምንም ማረጋገጫ ቢቢሲ ቀዳሚውን ስፍራ ወስዶ ሲያስተጋባው እንደነበር በአብነት ማውሳት ይቻላል፡፡

ነገር ግን ልክ እንደሰሞኑ በወቅቱ ሂዩማን ራይትስዎች የተባለው ፅንፈኛ ኒዩ - ሊበራል ተቋም "የኢትዮጵያ መንግስት ዕርዳታን ለፖለቲካ መሳሪያነት እየተጠቀመበት ነው" በማለት ያወጣው የተለመደ የቅጥፈት መግለጫን፤ ሀገራችን በስራው ላይ የተሰማሩትና በምህጻረ ቃል "ዳግ" (DAG) እየተባሉ የሚጠሩት ከ20 በላይ የልማት አጋር ቡድን አባላት ባደረጉት ጥልቅ የማጣራት ስራ የእርዳታ እህል ለፖለቲካ ጥቅም መዋሉን ማረጋገጥ አልቻልንም፣እርዳታው " በማለት የፅንፈኛውን "ድርጅት" ውሸታምነት የዓለም ህዝብ እንዲያውቀው በአደባባይ ተናግረዋል፡፡

መቼም የዚህ ጽሑፍ አንባቢ በዚህ ወቅት የቢቢሲ አቋም ምን ሊሆን እንደሚችል መገመቱ አይቀርም፡፡ አዎ! የእንግሊዝ መንግስት የልማት አጋሮቻችን

ጭምር በሚገኙበት "ዳግ" አማካኝነት የፈጠራ ሪፖርቱ የተጋለጠው አክራሪው ኒዩ - ሊበራል ተቋም ከእንግዲህ ውሸቱ ይፋ መወጣቱን ቢቢሲ ተገንዝቧል፡፡ እናም እርሱን አሁንም ጠቅሶ ዘገባ ማቅረቡ ተቀባይነት እንደሌለው አውቋል፡፡

ሆኖም ሌላ ዘዴ መፈለግ ነበረበት። የሁለቱ ተቋሞች ትስስር "አፍንጫ ሲመታ፣ ዓይን ያለቅሳል" እንዲሉት ዓይነት በመሆኑ፤ ከእነ ሂዩማን ራይትስ ዎች ጋር ተነጋግሮ "ቱሪስት በመምሰል ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቼ አገኘሁት" ያለውንና እነ ሂዩማን ራይትስ ዎች አምና ላይ ሞክረውት ያልተሳካላቸውን የማጥላላት ዘመቻ ያለ ሃፍረት ደግሞታል። ይህም ጣቢያው ከጋዜጠኝነት ተግባሩ ውጪ ሂዩማን ራይትስ ዎችን ተክቶ እየሰራና አጀንዳውንም በዘገባ መልክ እያራመደለት መሆኑን አፍ አውጥቶ የሚናገር ተግባር ነው፡፡

እርግጥ ማንም ቢሆን አግባብ ባለውና ዕውነት ላይ በተመረኮዘ መንገድ መንግስት መተቸት የለበትም የሚል አቋም የሚኖረው አይመስለኝም፡፡ እንደ ቢቢሲ ዓይነት "ለጋዜጠኝነት ጥብቅ አሰራር ቆመናል" የሚሉ ሚዲያዎች መልሰው የራሳቸውን መርህ ሲጥሱ ማየት ከማሳዘን አልፎ የሚያሳፍር ተግባር መሆኑ ግን አያከራክርም፡፡

ጣቢያው "የኢትዮጵያ መንግስት ዕርዳታን ለፖለቲካ ፍጆታ ያውላል" በማለት ሂዩማን ራይትስ ዎች ቀደም ሲል ሞክሮት "ቀጣፊ" የተባለበትን የውሸት ዘገባ ብቸኛ ምንጮች ያደረጋቸው ወገኖች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሀገሪቱን ከጀርባ በጦር ከመውጋት የማይመለሱት ሦስት የመድረክና አንድነት አመራሮች መሆናቸው እንዲሁም ለይስሙላ በጥቂት የአየር ሰዓት ሽፋን እንግሊዝ ለሚገኙት የኢትዮጵያ መንግስት ቋሚ መልዕክተኛ ቡድን ምክትል ኃላፊ ለአምባሳደር አብዱረሺድ ዱለኔ (ለአንድ ሰው ብቻ መሆኑን ልብ ይሏል!) ዕድል በመስጠት በጋዜጠኝነት ሙያ የማዕዘን ድንጋይ የሚባለውን "የሚዛናዊነት" አሰራርን ሆን ብሎ በይፋ ጥሷል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ "ቢቢሲ በምርመራ ጋዜጠኝነት አሰራር ህግ መሰረት ሀገር ውስጥ ከገባ በስራው ላይ የተሰማሩትን የውጭ የልማት አጋር ቡድኖችንና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ለምን አላነጋገረም?' የሚል ጥያቄም ስናነሳ፤ የምናገኘው ምላሽ ጣቢያው ይዞት የተነሳውን ዓላማ የሚያረጋግጥልን ይሆናል፡፡

ይኸውም ገና ከጅምሩ የሂዩማን ራይትስ ዎችን አጀንዳ ለማራመድ እንጂ፣ ዕውነታን ለመዘገብ ወደ ኢትዮጵያ አለመምጣቱን ነው፡፡ ምክንያቱም ዘገባው ትክክል ቢሆን ኖሮ፣ ቢያንስ በ "ዳግ" ውስጥ ያሉትን የእንግሊዝ መንግስት ተወካዮችን እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተለያዩ የመንግስት አካላትንና የህብረተሰብ ክፍሎችን ያነጋግር ነበር፡፡

ከዚህ በተጨማሪም፣ቢቢሲ ያለውና ዕርዳታው ለፖለቲካ አጀንዳ የሚውል ቢሆን ኖሮ፣ አጋጣሚውን ካገኙ ሀገራቸውን ከመሸጥ የማይመለሱት ጨለምተኛ ተቃዋሚዎችና የደርግ ስርዓት ናፋቂዎችን ብቻ በተጠቀሰው የደቡብ ክልል በዋቢነት ከመጠቀም ይልቅ ፣ ሰሞኑን አልጀዚራ የተሰኘው የቴሌቪዥን ጣቢያ የሰራውን የልማት ተግባራት ዘገባን ለማየት በታደለ ነበር። ሆኖም ፍላጎቱ ለአንድ አመት ያህል የምርመራ ጋዜጠኝነት ቢሮ ከተባለው አካል ጋር በገንዘብ እየተሞዳሞደ የሀገሪቱ ገፅታ ላይ ጥላሸት መቀበቀት በመሆኑ፣በክልሉ ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለው የአልጀዚራ ዓይነት ልማታዊ ክንዋኔዎችን በተመለከተ ነበር።

ነገር ግን "አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም" እንዲሉ በመሆኑ፣ አመጣጡ ልቦለዳዊ ድርሰትን ቀምሮ ለመሄድ ስለሆነ ይህን ማድረግ አልፈለገም፡፡ ከዚህ ይልቅ ዘገባውን ሆን ብሎ በማይታመኑ ምንጮች (Anonymous Sources) በማጨቅ ብሎም በስም ያልተገለፁ የፈጠራ ቀበሌዎችንና መንደሮችን በማካተት ተዓማኒነት የሌለው እንዲሁም ከዕውነታው የራቀ መሰረተ - ቢስ ታሪክን በማዘጋጀት የሂዩማን ራይትስ ዎችን የሀገር ውስጥ ውድቀት በቀጣፊነት ሊያካክስለት ተሯሩጧል - ምንም እንኳን ሃሳቡ ከቀቢፀ - ተስፋነት ሊዘል የማይችል ቢሆንም፡፡

ሌላው እጅግ ያስገረመኝ ጉዳይ፣ የቢቢሲን የውሸት ዘገባ ሲያስተዋውቅ የነበረው የጣቢያው አንባቢ ኢትዮጵያን "የአንድ ፓርቲ ስርዓት ሀገር" ሲል ማዳመጤ ነው፡፡ እንግዲህ ይታያችሁ! ይህ የአንባቢው አባባል የሐሰት ታሪኩ ማጠናከሪያ መሆኑ ነው፡፡ ዳሩ ግን ሀገራችን ውስጥ እንዲህ ዓይነት "ስርዓት" አለመኖሩን ዓለም የሚያውቀው ሃቅ መሆኑም ማን በነገረው?

የአንድ ፓርቲ ስርዓት በሀገሪቱ ህዝቦች መራር ትግል ግብዓተ - መሬቱ ከተፈፀመ ድፍን 20 ዓመታት አልፈውታል፡፡ በምትኩም የመድብለ - ፓርቲ

ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ተፈጥሮ የሀገሪቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የስልጣናቸው ባለቤት ሆነዋል፡፡ በዚህም ላለፉት አራት ዙሮች የመብታቸው ተጠቃሚ ሆነው እጅግ በርካታ ቁጥር ካላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ያሻቸውን በመምረጥ፣ የማይፈልጉትን ደግሞ ድምፃቸውን በመንፈግ ስልጣናቸውን በዴሞክራሲያዊ መንገድ እየተገለገሉበት ነው፡፡

እንደሚታወቀው የአንድ ፓርቲ ስርዓት አምባገነናዊ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ስርዓት ደግሞ ለቢቢሲዎች ብቸኛ የውሸት ምንጮቻቸው የሆኑትን የመድረክ አመራሮችን ዓይነት ተቃዋሚ እንዲደራጅ የማይፈቅድ ከመሆኑም በላይ፤ ማንኛውንም ፀጉረ - ልውጥ ሀገር ውስጥ ሲያገኝ በጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል በዓይነ - ቁራኛ የሚመለከት ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲህ ዓይነት ስርዓት ቢኖር ኖሮ፤ "በቱሪስትነት ገብተናል" ያሉት የእነ ሂዩማን ራይትስ ዎች "አምባሳደሮች" የሀገሪቱን ስም ለማጎደፍ የተሰለፉ ተቃዋሚዎችን መጠየቅ ብሎም የትም ቦታ ሄደው እንዲዘግቡ አይፈቀድላቸውም ነበር፡፡

ይህን እንጂ ሀገራች ውስጥ ያለው መንግስትም ሆነ ስርዓቱ ዴሞክራሲያዊ በመሆኑ፤ ተቃዋሚዎች ውሸትም ቢሆን ያሻቸውን የሚናገሩበት እንዲሁም እነርሱን ጨምሮ የውጭ ዜጎች እንደልባቸው እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን ሊገነዘቡት በተገባ ነበር፡፡ ምንም እንኳን የቢቢሲዎች ነገር አሁንም "አውቆ የተኛን ..." እንዲሉት ቢሆንም፤ እንዲህ ዓይነቱን ስርዓት ከቻሉ ኤርትራ ሄደው ማየት ያለባቸው ይመስለኛል፡፡ እነርሱ አብጠርጥረው እንደሚያውቁት፤ በአምባገነናዊ ስርዓት የምትማቅቀው ሀገርን ባህር አቋርጠው ወደ ምጽዋ ለመዝለቅ የሞከሩ ስድስት እንግሊዛዊያን፤ በጸጉረ - ልውጦች ላይ በሚደረግ ጥብቅ ቁጥጥር እንዲሁም በአፈና መዋቅሩ ሳቢያ "ሰላይ" ተብለው ምን ዓይነት ዕጣ ፈንታ እንደገጠማቸው በግልጽ ይመለከቱት ነበር፡፡

ለነገሩ የቢቢሲ አውቆ የመተኛት አባዜ ሰሞኑን የመጣ ልማድ አይደለም። የዛሬ ዓመት ገደማ ጣቢያው በ1977 ዓ.ም በተከሰተው ረሃብ በወቅቱ የህዝቦችን መሰረታዊ ጥያቄ አንግቦ መታገል ላይ የነበረውን ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) "የዕርዳታ እህልን ለጦር መሣሪያ ግዥ አውሎታል" የሚል የፈጠራ ዘገባ አቅርቦ፤ ብዙም ሳይቆይ የዕርዳታው አስተባባሪ የነበሩትን ሰር ቦብ ጊልዶፍን

“ተሳስቻለሁ” በማለት ይቅርታ ጠይቋል፡፡ ሆኖም ሆን ብሎ የጉዳዩ ባለቤት የሆነውን የኢትዮጵያን መንግስት ምንም ዓይነት ይቅርታ ለመጠየቅ አልፈለገም፡፡

ይህም ጣቢያው ለእነ ሂዩማን ራይትስ ዎች ያለውን ታማኝነት ለመግለጽ የተጠቀመበት የወገንተኝነት ዘዴ እንደሆነ ከማንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ታዲያ ይህ ተግባሩ “እውን ቢ.ቢ.ሲ. ሚዲያ ነው ወይስ ‘ለትርፍ ያልተቋቋመ’ ሲቪክ ማህበር?” አያስብልም ትላላችሁ?- አዎ! ጣቢያው በእንግሊዝ ህዝብ ግብር እየተዳደረ፣ በተግባር ግን “ኃላፊነቱ የተወሰነ የእነ ሂዩማን ራይትስ ዎች የግል ማህበር” ላለመሆኑ ማንም በእርግጠኝነት ሊናገር አይችልም፡፡

ስለ ቢ.ቢ.ሲ. ይህን ያህል ካልኩ ዘንዳ፤ የፈጠራው ታሪኩ ብቸኛ ምንጭ በመሆን ራሳቸው ጠቋሚና መልስ ሰጪ የማድረግ ድራማን ወደ ከወኑት የሀገራችን ተቃዋሚ ተብዬዎችና በህዝብ ካርድ ስለተተፉት ጉደኞች ላምራ፡፡ ለህዝባቸው ሳይሆን ከመድረኩ ጀርባ ሆኖ ድራማውን ለፈበረከው ሂዩማን ራይትስ ዎች ታማኝ ተላላኪ ሆነው ለዓመታት ያገለገሉት እነዚህ ስለማያውቁት የኒዩ-ሊበራል አጀንዳ የሚቀለቀምዱ ወገኖች፣ የልቦለድ ዘገባው ስጋ የለበሱ ገጸ - ባህሪያት ሆነው ብቅ ብለዋል፡፡ ስማቸውም ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ፣ ዶክተር መረራ ጉዲና እና ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ይሰኛል፡፡ እርግጥ እነዚህን የጨለማ ዓለም ሰዎችን ማንነት ለማወቅ ሊቅ መሆን የሚያስፈልግ አይመስለኝም፡፡ ማንነታቸውን ለባዕዳን ያደረው ፀረ - ሀገር ተግባራቸው በይፋ ይናገራልና፡፡

የዚህ ጽሑፍ አንባቢ እንደሚያውቀው፣ እነዚህ ሦስት የመድረክና የአንድነት አመራር ተብዬዎች ለህዝባቸው ከአመፅና ከሁከት ቆስቋሽነት አስተሳሰብ ውጪ ጠብ የሚል አንዳች ነገር ሊያመጡለት ስላልቻሉ፣ ከምርጫ 97 ጀምሮ በህዝቡ ሚዛናዊ ውሳኔ በዝረራ ተሸንፈው እስካሁን ድረስ ከወደቁበት መነሳት የተሳናቸው ጉዶች ናቸው፡፡ ታዲያ ከወደቁበት ለመነሳትም ሀገራቸውን በመካድ የሂዩማን ራይትስ ዎች ተላላኪ መሆንን የመረጡና በሰላማዊው ምህዳር ውስጥ እየተንቀሳቀሱ የውሸት ወሬ አቀባይነትና ጆሮ ጠቢነትን በፖለቲካ ስልትነት ይዘው የሚንቀሳቀሱ ፀረ - ህዝብ ኃይሎች መሆናቸው ከማንም የተሰወረ ሃቅ አይደለም፡፡

'ምናልባት አክራሪ ኒዩ - ሊበራሎቹ ስልጣን ላይ ያወጡን ይሆናል' በሚል 'ላም አለኝ በሰማይ ...' ዓይንት ቅዥት ሀገር ውስጥ ቁጭ ብለው የማያቀነባብሩት የፈጠራ ወሬ የለም፡፡ ጽንፈኞቹም ቀደም ሲል የጠቀስኩትን የፖቲካ አጀንዳዎችን ለማሳካት እነዚህን ወገኖች የውሸት ጥርቅምቃሚ አባባሎችን በመቃረም ያለምንም ተጨባጭ ማስረጃ የመግለጫ ጋጋታ ያወጣሉ፡፡ ይሁንና መግለጫዎቹና ሪፖርቶቹ እነዚህን ወገኖች ከመሳለቂያነት ባለፈ የህልም እንጀራቸው የሆነውን "ዙፋን" ሊያስገኝላቸው አልቻለም፡፡ ምክንያቱም በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ በውጭ ኃይሎች የሚዘወር ዴሞክራሲም ሆነ ስልጣን ባለመኖሩ ነው፡፡

የመድረክና የአንድነት አመራሮች የሚመሩት የብሶት ፖለቲካን በማራመድ አጀንዳ በመሆኑ፤ አንድ ነባራዊና ክስተት በተፈጠረ ቁጥር ጉዳዩን ባልተከተሰበት መልኩ ለእነ ሂዩማን ራይትስ ዎች ማቀበል "የዕለት እንጀራቸው" የሆነው ዛሬ አይደለም፡፡ በሚመሯቸው አባላት ዘንድ በፍጹም አምባገነናዊነታቸው የሚታወቁትና "የቀለም አብዮት አባት" እየተባሉ የሚጠሩት ፕሮፌሰር በየነ እንዲሁም በጠባብነታቸው፣ በጭፍን ፖለቲከኛነታቸውና የሀገሪቱና የህዝቦቿ ጠላት ለሆነው የኤርትራ መንግስት ጠበቃ ሆነው ይከራከራሉ የሚባሉት ዶክተር መረራ የአክራሪ ኒዮ - ሊበራሎች "የሀገር ውስጥ አርበኛ" ሆነው መስራት ከጀመሩ የአንድ ወጣት ዕድሜን ቅርጥፍ አድርገው የበሉ ናቸው ፡፡

የአምባገነኑ የደርግ ስርዓት ባለሟልና በአንድ ወቅት የሌተና ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም አማካሪ ነበሩ የሚባሉት የዛሬው የአንድነት ፓርቲ የጎዳና ላይ ተደባዳቢው እንዲሁም ብህዝቦች መራር ትግል የተገኘውን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግልፅ ጠላት በመሆን "ህገ-አራዊት ነው" በማለት በይፋ ሲዘልፍት የነበሩት ፕሮፌሰር መስፍንም 'የጠላቴ ጠላት... " በሚለው ብሂል የሚመሩና በውሸት መረጃ አቀናባሪነት የተሰለፉ ግለሰብ ናቸው፡፡

ለአንባቢዎቼ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ፤ እነዚህ የመድረክ አመራሮች በቅርብ ጊዜ ውስጥ የሂዩማን ራይትስ ዎች ተላላኪ የሆኑበትን እንዲሁም ውሸታቸው የተጋለጠበትን ተግባር ማየቱ ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡ ...ጊዜው በምርጫ 2002 ዋዜማ አካባቢ ነው፡፡ ሂዩማን ራይትስ ዎች የተባለው አክራሪ ተቋም "የኢትዮጵያ

መንግስት ዕርዳታን ለፖለቲካ ማራመጃነት እየተጠቀመበት ነው” የሚል የተለመደ የቅጥፈት መግለጫውን ያወጣል፡፡

የመግለጫውም ዋቢዎቹ ሀገር ውስጥ የሚገኙት የመድረክ አመራሮች መሆናቸውን በወቅቱ ይፋ ያደርጋል፡፡ ይሁንና ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት “ዳግ” የተባለው የልማት ደጋፊ ቡድን ዕርዳታ ለፖለቲካ ፍጆታ አለማዋሉን በማጣራት ማወቁን ይፋ ያደርጋል፡፡ ታዲያ እነዚህ ወገኖች በወቅቱ ‘ለምን የጡት አባታችን ተነካብን ‘ በሚል አሳፋሪ ፀረ - ሀገር አመለካከት፣ ውሸታቸውን ለማድበስበስ መሞከራቸው በርካታ ሀገር ወዳድ ዜጎችን ያስደመመ ድርጊት ሆኖ አልፏል፡፡

እነዚህ ወገኖች በሰሞኑ የቢ.ቢ.ሲ የፈጠራ ዘገባ ላይም፣ በውሸት ምንጭነት መሳተፋቸው የሂዩማን ራይትስ ዎችን ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕዛዝ ለመፈጸም መሆኑን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ ልዩነቱ የሀገር ውስጥ ተላላኪው ቡድን እንደቀድሞው ለቀጥታ የውሸት ዲስኩሩን ለአክራሪው ኃይል ከመስጠት ይልቅ፣ ቢ.ቢ.ሲ ለተባለው ሌላኛው የውጭ ሀገር ተላላኪ መቀላመዱ ነው፡፡ በዚህ ፀረ - ህዝብ ተግባራቸውም እንዳለፉት ጊዜያት ሁሉ፣ ‘ለህዝቡ ዕርዳታ እንዳይሰጠው’ የሚል አንድምታ ያለውን የፖለቲካ አጀንዳ እያራመዱ የባንዳነት ተልዕኮቸውን እየተወጡ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ምንም እንኳን እነዚህ ወገኖች የሀገርን መልካም ስም ለማጉደፍ በክህደት ጎራ ተሰልፈው “መንግስት ዕርዳታን ተቃዋሚን ለሚደግፉ አካላት አይሰጥም” የሚል ፍጹም ከኢትዮጵያ መንግስት ተፈጥሮአዊ ባህሪ ጋር የማይሄድ መግለጫን “የአይጥ ምስክር ድንቢጥ” ሆነው ለቢ.ቢ.ሲ ቢሰጡም፣ በተጨባጭ ሀገሪቱ ውስጥ ያለው ተግባር ግን እነርሱ እንደሚዘላብዱት አይደለም፡፡ በመጀሪያ ደረጃ መንግስት ለሁሉም የሀገሪቱ ዜጎቹ ኃላፊነት የሚሰማው አካል መሆኑን ከጥላቻ አስተሳሰብ ወጥቶ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

የዕርዳታ እህልን ደጋፊና ተቃዋሚ በሚል እየከፋፈለ የሚሰጥበት አንዳችም ምክንያት የለውም - ከህዝብ አብራክ የወጣና ለህዝብ የወገነ ኃይል ነውና፡፡አንድ ዴሞክራሲያዊ መንግስትም “የመረጠኝ እና ያልመረጠኝ” እያለ ሞራላዊ ሃላፊነቱን የሚዘነጋ አይደለም።ይልቁንም ያልመረጠው ህዝብ ለቀጣይ እንዲመርጠው ተግቶ

ይሰራል።የኢትዮጵያ መንግስትም ከምርጫ 97 ጀምሮ ሲያደርግ የነበረው ይህንኑ ነው-አዲስ አበባ ላይ ተሸንፎ ኋላ ላይ ያሸነፈበትን ዕውነታ ልብ ይሏል!

ያም ሆነ ይህ ተቃዋሚዎቹ "የቁራ ጩኸት" የለየለት ቅጥፈት መሆኑም ተረጋግጧል፡፡ ራሳቸው ፕሮፌሰር በየነ "ይደግፈኛል" እያሉ የሚደሰኩሩበት ነገር ግን በምርጫ 2002 የተሸነፉበት በደቡብ ክልል የሚገኘው የትውልድ መንደራቸው ነዋሪዎች ሳይቀሩ፤"መንግስት ዕርዳታ የሚያከፋፍለው ደጋፊና ተቃዋሚ እያለ አይደለም፡፡ ለሁላችንም የሚደርሰንን ያህል ያለምንም አድልኦ እየሰጠን ነው" ብለዋል፡፡ በወላይታና በሌሎች የክልሉ አካባቢዎችም ተመሳሳይ ዓይነት የህዝብ አስተያየት ተደምጧል፡፡ ታዲያ ፕሮፌሰር ተብዬዎቹ ጨለምተኛ ተቃዋሚዎች የት ባዩት እውነት ነው እንዲህ ዓመታቸውን ጠብቀው የተላላኪነት ስራቸውን ለመከወን ዓይናቸውን በጨው ታጥበው የሚዋሹት?...

ታዲያ እዚህ ላይ ኒዩ-ሊበራሎች የሀሰት አታሞአቸውን በደለቁ ቁጥር አብሮ "አሸሸ ገዳሜ" በሚል ዘፈኑ የሚታወቀው የአውራምባ ታይምስ ጋዜጠኛ ተብዬና 97 ዓ.ም ላይ ተቸንክሮ የቆመው ተቃዋሚ ፖለቲከኛው አቶ ዳዊት ከበደ በቅጥፈት አዳማቂነቱ ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይደለም። ሰሞኑን የእነ ቢቢሲን "ትክክለኛነት" አስመልክቶ በርዕሰ አንቀፁ አቋሙ አድርጎና በፊቸር ፅሁፉ የዘገባ ሃቀኝነት በጥፍን ጥላቻ ለመመስከር መሞከሩ ዛሬም እንደለመደው እውነታን ሳይሆን ስሜቱን ለመዘርገፍ መሯሯጡን የሚያሳብቅበት ነው።

በተቃዋሚነት ጭንብል ተጀቡኖ የጥላቻ ፖሊቲካን በማራመድ ነገሮችን ሳያጣራ ህዝብን ለማሳሳት መጣር ምን ዓይነት ጋዜጠኝነት መሆኑ ለዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ግልፅ ባይሆንም፤ ነገሩን በጥሞና ለሚያስበው ሰው ግን ግለሰቡ ከዚህ ቀደም የአክራሪ ኒዩ-ሊበራሎች "ጉዳይ ፈፃሚ" በመሆን ተሸላሚ ስለሆኑ የበሉበትን ወጪት ላለመስበር የሚያደርጉት ርብርብ መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም።

እርግጥ የዚህ ጽሑፍ አንባቢ የውሸቱ "አዝማች" እነማን እንደሆኑ ተንዝቧል የሚል እምነት አለኝ-ተላላኪዎቹም ለእነማን እንደሚሰሩ ጭምር። አዎ! በተላላኪነት የተሰለፉት የውጭው ቢቢሲም ይሁን፤ የሀገር ውስጥ "አርበኞቹ" የመድረክና የአንድነት

አመራሮች  እንዲህም በፕሬሱ ውስጥ የተወሸቁ አንዳንድ ወገኖች የሚሰሩት እነ ሂዩማን ራይትስ ዎችን ለመሳሰሉ ፅንፈኛ አክራሪዎች ድብቅ የፖለቲካ  አጀንዳን  ለማስፈጸም ነው፡፡ ይሁንና “እውነትና ንጋት  እያደር ይጠራል” እንዲሉ፤ የእነዚህ  ኃይሎች የትናንት ቅጥፈታቸው በራሳቸው በይቅርታና ውሸት እንደተጋለጠው  ሁሉ፤ ሰሞነኛው የፈጠራ  ልቦለድ  ድርሰታቸውም  እርቃኑን የሚወጣበት ጊዜ ሩቅ  የሚሆን አይመስለኝም፡፡